ጾመ ሁዳዴ ለምን 55 ቀን ይጾማል?

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ሥርዓት በየጉሙቱ ከሚመላለሱት አጽዋማት መካከል ታላቁ / ዐቢይ/ ጾም ዘንድሮ የካቲት ፲፭ /፲፱፻፹፫ ተጀምሮ ሚያዝያ ፱ ፲፱፻፹፫ ይፈጸማል ። "ሁዳዴ" በመባል የሚታወቁና በመንግሥት ይዞታ የሚከለሉ ሠፋፊ መሬቶች ነበሩ የሚታ ረሱትም በአርሶ አደሩ ኅብረትና ጉልበት በትዕዛዝና በአዋጅ ነው ። በዚሁ አንጻር ዐቢይ ጾምም የጾምን አስፈላጊነትና ሕጋዊነት ተቀብለው በሚጾሙ ክርስ ቲያኖች ሁሉ ቤት ወንድ ልጅ አዋቂ ሳይባል ከሊቅ እስከ ደቂቅ የሚጾ ሙት ፣ የዓለም መድኀኒ ኊታችን መድ ኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቆሮን ቶስ ገጻም ጾሞ የነለምን ተፈታታኝ ክፉ መንፈስ ከነፈተናው ድል የነሳበት በመሆኑ ሁዳዴ ዐቢይ /ታላቅ/ጾም ተብ ሏል ። በዚህ ጾም ሰሰት ታላላቅ የኃ ጢአት አበጋዞች / አርአስተ ኃጣውሕ /

ድል ተነስተ ውበታል ። በመብል ምክንያት ወደ ዓለም የገባው ኅጢአትና ኃጢአት ያስከተለው ሞት ከሥራቸው ተነቅ ለው ተጸምሰው ፣ የጠፋው የሰው ሕይወት ታድሶበታል ። ሰው በሥጋዊ መብልና መጠጥ ብቻ ሰውነቱ የሚያ ምር በጾም የሚጠወልግ የሚኮሰ እየ መሰላቸው ጾምን የሚፈሩት የሚሸሹት ጥቅም እንደማይሰጥ ሰው ሠራሽ ሥር ዓት አድርገው የሚመለከቱትም ሞል ተዋል ። አስተዋዮች ግን ሰው ከእግ ዚአብሔር እና በሚወጣ ቃለ እግ ዚአብሔር ቁምር እንጂ በአዕል ሙሀ ብቻ ሊኖር እንደማይችል ጠንቅቀው አውቀው እየጾሙ ይጠቀሙበታል ። አስፈላጊም በሆነ ቦታ ጊዜ ከማይፈ ልግ ጮማ ወይን ይልቅ ጥራጥሬ ተመ ገብ መውሣት ማማር እንደሚኖር ከሶ ስቱ ወጣቶች / እናንተ ፣ አህረያ ሚሳ ኤል / ታሪክ መገንዘብ ይቻላል ። /ዳን.፩ ፍ-፲፮ /

የቤተ ክርስቲያን ሥርዓትና ደን ጋጌ (የሕግ ምንጭ) በሆነው ፍትሐ ነገሥት ፣ ስለጾም በተመለከተው አን ቀጽ እንደተገለጸው ጾም ፣

—ጾመ ሕግ ኃይማኖታዊው የተና ፪ፍ፲ሸ የኢትዮ ጉባዔ ሊታ ውነት አበው በመስጉት

መሠረት ፍትሐ ነገሥት እንተጽ ፲ሸ የተመለከቱትና ክርስቲያኖች ሁሉ እንዲጾሟቸው የታዘዙት ፣

እነዚህ አጽዋማት የየራሳቸው የሆነ ታሪክና ትንታኔ ያላቸው ሲሆኑ ፣ ሁሉም ያለ ልዩነት በሁሉም ክርስቲያኖች በይፋ በሚገባር እንዲጾሙ የተወሰኑ ናቸው ።

ጾመ ፈቃድ በገል ውሳኔ በኃጢ አት ሰሜት የሸከረ ኅሊናን ለማጥራት ወይም የትድስናን ጸጋና የበለጠ መንፈ ሳዊ ክብር ለማግኘት በመሞከረ ንስሐ አማካይነት አስዘያም ብቻ ለብቻ በሥ ውር ዐይቶ በግልጽ የሚፈጽ ለማ አምላክ የሚተርብ ነው ።

ዐቢይ ጾም ለምን ፶ቱ ቀን ሆነ ?

በሁዳዴ/ ዐቢይ / መገቢያና መረጃ ሚያ የሚጾሙ ሁለት ዓምንታት አሉ ። የመጀመሪያው ዝመረጃ(ጾመ ሀጊታል) ነው ። የመጨረሻውም ሕማማት የተ ሰኘው ነው ። ሁለቱም በቂ ምክንያቶች አሏቸው ። ከነሱ በፊት የሚጾም የነ ነቢ ጾምም አለ የሰሰት ቀናት ጾም ነው ጠቅላላ ታሪኩ በትንቢተ ዮናስ የተገለጸ ስለሆነ መመልከት ይቻላል ። እኛ የነነዌን ጾም የምንጾመው የነነዌ አገር ሰዎች በነቢዩ ዮናስ አሳብነት የሰሰት ቀናት ጾም ኅዘን አድርገው ሲያጠፉት ከመጣ ጥፋት በመዳናቸው የቀኖና የተነሳሕያን የንስሐ አብነት (በጐ ምሳሌ) ስለሆኑ አበው ሐዋርያት እንዲጾም ወስነውት የኖም አባቶች ተቀ ብለውት ሲጾም ኖሮአል ። ከዘይሳችንም ብዛት አኳያ ብንመለከተው ለምሕረት ይቅርታ የነነዌ ዐይነት ጾምና ንስሐ በየግዜው ያስፈልገናል ።

ፍቅ የተባለ ንጉሥ አገዛዝ አጽ ንቶባቸው በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ምእ መናን ሠርቃል እንዲረዳቸው በጠየቁት ጊዜ ለመርዳት ፈቃደኛ ቢሆንም ሐሣ ርያት ሰው የገደለ ሰው እድሜውን ሙሉ እንዲጾም ስለወሰኑ ወጉዳዩ የሚ ቸገርበት መሆኑን ገለጸላቸው ። ሕዝ ቡም ያንድ ሰው እድሜ ሰባ ስማኒያ ነው እኛ እንጾምልሀለን ዝምተህ ጠሳ ታችንን አስወግድልን ስላሉት ታላቁ ውን ተቀብሎ ችግራቸውን አስወግዶ ሳቸዋል ። እነሱም አምስት አምስቱን ቀን ተካፍለው ጾመውለታል ። ያላወ ቁት እንድ ጊዜ ፣ ያወቁት ሐሣርያት ጾሙ ብለው ሥርዓት አድርገው በያ መቱ የሚጾሙት ብነዋል ። አበው ሐዋርያት ከትምህርተ ወንጌል ሥምራት አስቀድሞ አምስት አምስት ቀን ያመ ጾም ልማድ እንደነበራቸውም ታው ቋል ። ሌላው የጾመ ሠርታል ምክን ያትም በሚው ዐቢይ ጾም ቀናት ውስጥ የሚገኙ ዕለታተ ሰንበትን የሚተካ ነን ይሆን ተገልጾአል ።

ሌሎው ከሆነኑና እስከ ትንሣኤ ያለው ሰመኑ ሕማማት ነው በሕማማት ሰሞነ የኅሳም መድኃን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው ልጆች ደኅንነት ሕማምም መከራ የተቀበለባት ፡ በመስቀልም የሞትን ጽዋ ተቀብሎ ሰሞት ኃጢአት ከመገባት ነፃ ያደረገን ስለሆነ ሕማሙን ፡ ምክረ ሞቱን ሰኛ ሲል የተቀበለውን ፀዋትው መከራ በጾም ፡ በጸሎት ፡ በስጊድ ፡ በገዝነ ሰማ ሰብ በቤተ ክርስቲያን አበው የተወሰነ በመሆኑ ነው ።

ማንኛውም ክርስቲያን ''ጾም ዘና ንተ ዘንድ የከበረ ይውን '' ብለው የዓ ሰም ብርሐናት ብፁዓን ሐዋርያት በዲ ድስቅሊያቸው ፤ አንቀጽ ፲፱ በወሰነት መሠረት ከጥሉላት መባልዕት ፡ ሥጋ ፡ ቅቤ ፡ ውሃት ፡ ዓሣም ሳይቀር ፡ ተከል ከሉ አጽዋማትን እንዲከታተል ግዴታ አለበት ።

አክፍሎት የሚባለውም ሐዋር ያው ያዕቆብ ስለንታችን ሞትና መቃ ብር እገሪ እስከ ትንሣኤው ብርሃን የጾመውን አብነት እድርገው ሐዋር ያት ትንሣኤውን ሳናይ እህል እንቀም ሰም ብለው ስለጾሙት ብዙ ምእመናን ከሐሙስ ማታ እስከ እሑድ ሌሊት ፡ እንጸንዶችም እስከ ዓርብ ማታ ፡ ሁለ ትና ሶስት ቀናት ያከናሳሉ ።

''ጾም ማለት ምን ማለት ነው?''

በቤተ ክርስቲያናችን እምነትና ትም ህርት ጾም ማለት የሰው ልጅ ሕይወ ትን ለሰጠው የሕይወትን መመሪያ ሳዘጋጀለት ፈጣሪ እየታዘዘ ፡ ኃጢአትን ለማስተሰረይ ፡ የምትት ፍትወትን ኃይል እድክሞ ሥጋ ለነቢብ ነፍስ ትገዛባት ዘንድ በሕገ በታወቁ ጊዜያት ከመብል መጠጥ መከልከልና የመንፈስ ብርታት ማግኘ የተበብ መንገድ ነው ።

ጾም ጸሎት ምጽዋት የተያያዙ የስነ ምግባር ሰንሰለቶች ስለሆኑ በተ ግባር ተጠብቀው ሲተረጎሙ የእግዝ ሕይወት ከቅዱስ እግዚአብሔር ጋር ያያይዛል ። በአበው ሥርዓተ ሕማድ ማንኛውም ሥራ ሲታሰብ ሲታቀድ ሲጀመር ሲፈጸም በጾም በጸሎት ነው።

እነዚህን እንድነት የተሰበሰቡ መሣሪያዎች አጠንክሮ የሚጠቀምባ ቸው ክርስቲያን የኅግርን ጊዜ የሚለፍ ኃይል ይኖረዋል ።

—ጸሎት እምነት እንዲለመልም ፡ እንዲፋፋ እንዲያፈራ ይረዳል ፡ ጾም ደግሞ እምነትን ጸሎትን እያጠናከረ ብዙ ድንቅ ሥራዎች እንዲሠራ ያደ ርጋል ።

—ጾም ነፍስን በእግዚአብሔር ፊት ትሁት ያደርጋል ።

የሥጋን ፈቃድ አስገዝቶ ነፍስ እንድትነግ እንድትቀደስ አቋሟን እን ድታስተካክል ይረዳታል ።

ጾም ለነፍስ ብቻ ሳይሆን በሥጋ ሕይ ወትም ለሆድ ዕቃችን (ለሰውነታችን) የውስጥ የምግብ ማዘጋጃ ክፍሎች ዕረ ፍትን ይሰጣል ትሁትና ትን ያደርጋል

በሥጋዊ ፍላጎቶቻችን ፈቃዶቻ ችን ላይ አዛጋቸ መሆናችንና ያረጋግ ጥልናል ።

ለመንፈሳዊ ሕይወታችን ተቃራኒ በሆኑ ርኩሳን መናፍስትና በአጋንንት ላይ ኃይል እንድናገኝ ፡ ከፈተናዎች እንድንደን ይረዳል ፡ ክህደትን ጥርጥ ርን ያጠፋል ፡ እምነትንና ፡ እምነት የም ንሠራቸውን ሥራዎች ያጠናክራል ። የተበብን መንገድ የሕይወትን ጐዳና ይገልጣል ።

በጾም የተጠቀሙ አበው

እስከዛሬ በታለፈው የሐይማኖትና የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ በጾም በጸሎት ኃይል የተፈጸሙ ብዙ ታላላቅ ሥራዎች በነዚህ መሣሪያነት የተጠ ቀሙ ብዙ አበው በቅዱሳት መጻሕፍት ተመዝግበዋል ።

ሙሴ በሲና ተራራ ፵ ቀን ጾሞ ለሕይወታችን መመሪያ በእግዚአ ብሔር ጣት የተጻፉ አሥርቱ ቃላት ያለባቸውን ጽላቶች ተቀብሏል ። ሕገ ኦሪትን ሠርቶአል/ዘፀ.፴፬ ፡ ፳፰/

[illegible]

በሲና ተራራ ፵ውን የጾሙን ሱባኤ ፈጽሞ ጽላትን ከፈጣሪው ተቀብሎ በተመለሰ ጊዜ መላ ስሙነቱ ብርሃን ስለሆነ ሕዝቡ መልኩን በቀጥታ ማየት ስላልቻሉ እንዲሸፈንላቸው እስከ መለሙን ያድስዋል ። ዘፀ. ፴፬፡፳፱-፴፭/

፵ ቀን በምድያም ተወሰኖ ወገ ኖቹ እሥራኤልን ከባዕድ አገዛዝ ነፃ አውጥቶአል ።

እሥራኤልን ፵ ዘመን ሙሉ በሲና በረሃ ሲመራ ችግር እንዳይገጥ መው ጌታ እግዚአብሔር መና ከሥመና እያወረደ (ዘፀ.፲፮፡፪-፲፮/ ውሀ ከሥንጫ እያፈለቀ ዘፀ.፲፯፡፪-፯ ፤ መገበለታል ።

በሌት በፈቱ የሚሔድ መልአክ ሠይሞ ቀን በደመና ፡ ሌሊት በእሳት ብርሃን /ዕዮድ/እየመራ ምድረ ርስትን አመርሶታል ። ዘፀአ.፲፫፡፲፱፡፳፪፡፴፭ ።

ኤሊያስ ፵ ቀን ጾሞ በእሳት ሠረ ገሳ ፡ በአውሎ ነፋስ ተነጥቆ ፡ ወደ ገነት አርጓል ። ፩ ነገ.፲፱፡፰፡፲፪ ነገ.፪፡፲፩ /ሰሞት አልተገኘም ።

ዕዝራ ፵ ቀን ጾሞ የጥበብ የሕይ ወት መመሪያ መጻሕፍትን ጽፎአል። /ዕዝ.፯፡፮/

ነቢዩ ዳንኤል ከሀገሩ ከኢየሩሳ ሌም በምርኮ በተወሰደበት ሀገር በአ ንድ አምላክ ላይ ከነበረው ጽኑ ዕም ነት ሳያወላውል በጾም በጸሎት ተወ ስኖ በመገኘቱ ፡

ከአንበሶች እፍ እንደዳነ

ሕልምን የመተርጐም ዕውቀት ጥበብ እንደተሰጠው ፡

ሀገሩ ኢየሩሳሌም ነፃ የምትሆ ንበት ወገኖቹ እሥራኤል ከሰደት የሚመለሱበት ከዚህም በላይ ረቂቅና ጠለቅ ያለ የክርስቶስ ሰው የመሆን ምሥጢር እንደተገለጸለት በሱባኤው ፍጹሚ መሳእክት ተልከው እንዳረጋ ገጥ የምሥራች ዜና እንዳሰሙት ፈተና ውን ሁሉ ድል እንዳደረገ ተጽፎ አል ። /ዳን ፱፡፪-፴፡ ቁጥ-ጽ፪፡ም.፲፡፪-፲፪

የዓለም መድኃኒን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በገዳመ ቆሮንቶስ ፵ ቀን ፵ ሌሊት ጾሞ የዚህ ዓለም ተፈታታኝ የሆነ ዲያብሎስን ከነፈተናው ድል ነስቶአል ። በስስት በትዕቢት በፍቅረ ንዋይ የመጣውን ፈተና አጥፍቶ የኅ ጢአትን እቦሀ አቃጥሎአል ።

ስስት - ያልተሰጡትን መሻት የሌ ሎችን ሥርዓ በይዘልጥ ለመሻ ማት መሞከር

ትዕቢት -አምላክ እሆናለሁማለት በሌሎች ላይ ታላቅነትን (የበላይ ነትን) መመኘት

ፍቅረ ንዋይ - በታኝን አለማመቅ በተሰጡት አለማመስገን ነው ። እነዚህ አርእስተ ኃጣውዕ ይባላሉ ።

እያንዳንዳችን የልቡናችንን በር ከፍተን እንደገና ካላስገባናቸው በቀር ዘኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጾም ተወግደዋል ። ከሥሩ የተነቀለ ዛፍ እንዳይለመልም ፡ እንዳይዘራና እንዳ ያፈራ ኃጢአት በክርስቶስ ጾም ከሥሯ ተነቅላ ጠፍታለች በፍዳ የማታሲዝ ሆናለች ።

ጌታችን የጾሙን ሱባዔ ከፈጸመና በሰይጣን ተፈትኖ ድል ከነሳ በኋላ መላእክት ቀርበው ሰማዩውስታል ፡ ተገ ዝተውሰታል ፡ ኃይል ያንተ ነው ፡ ሥል ጣን ያንተ ነው እያሉ ምሥጋና አቅ ርበውሰታል ።/ማቴ.፬፡፲፩ ሉቃ.፭፡፲-፲፪/

እኛም በጾም በጸሎት ፡ በትዕግስት በንጽሕና ፈቃደ ሥጋን ፈቃደ ሰይጣ ንን ድል ብንነሳ የእግዚአብሔር መላእ ክት መጥተው እንደሚረዱን እንደሚያር ጋጉን እንደሚያጽናኑን የታመነ ነው ። (የሐሥ ፲፡-፲፡ ፴-፴፩)